# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ፕላንና ልማት ቢሮ

# የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት መመሪያ ቁጥር 178/2017 አጭር ማብራሪያ

2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## 1. መግቢያ

መንገድ የከተማ መዋቅር አካል እና የአንድን ከተማ ቅርጽ የሚሰጥ ነው፡፡ ከተገነባው የከተማ ክፍል መካከል ትልቁን ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ የተለያዩ የከተማ መሬት አጠቃቀሞች በተገቢውና በሚፈለገው መንገድ አገልግሎት እንዲሰጡ መንገድ ለሰዎች እና ለቁሳቁስ መዘዋወሪያነት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

የአንድ ከተማ የመንገድ ጥራት ደግሞ የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ የማሻሻያ አንዱ መሳሪያ ነው፡፡ በተጨማሪም መንገድ ለተለያዩ ተዛማጅ አገልግሎቶች ሊውል ይችላል (የመገበያያ ቦታነት፣ የመንገድ ላይ መናፈሻዎች፣ የመኖሪያ ቤት መዳረሻነት፣ የተለያዩ ፕሮግራሞች ማከናወኛ ቦታ፣ የመጫወቻ ቦታዎች ወዘተ…፡፡) እነዚህ ሁሉ በመንገዱ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ስነ-ምህዳራዊ እንዲሁም ፍልስፍናዊ አንድምታ ላይ የሚያሳርፉት ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናትን መነሻ በማድረግ ባለይዞታዎች ለሚያነሷቸው ቅሬታ ምላሽ መስጠት እና ለፕላን ፈጻሚ አካሎች ለአፈጻጸም ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላንና ልማት ቢሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (2) ተራ ፊደል (ሠ) እና በአዋጅ ቁጥር 52/2009 አንቀጽ 39(3) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

ይህንን መመሪያ ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት ስራው በባህሪው

- ❖ በየወቅቱ አዳዲስ የመሬት ዝግጅት /ሽንሻኖ/ የሚከናወን በመሆኑ፣
- ❖ የይዞታ ይካፈልልኝና ይቀላቀልልኝ እንዲሁም መብት ያልተፈጠረላቸው ይዞታዎች ስራው ባለመጠናቀቁ የመዳረሻ መንገድ ጥናት ጥያቄ በተለያየ ጊዜ እየቀረበ በመሆኑ፣
- ❖ አዲስ መንገድ ለማጥናት ሲሞከር ከዚህ ቀደም በስራ ላይ ያለው ማኑዋል ስራውን በሚፈለገው መንገድ ለማከናወን የተሟላ አለመሆን፣
- ❖ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ጥያቄ ያልተመለሰላቸው ባለይዞታዎች ቅሬታ መፍጠሩና የመልካም አስተዳደር ችግር በመሆኑ ክ/ከተሞች ለአፈጻጸም በመቸገራቸው እነዚህን የተዘረዘሩ ችግሮች ለመፍታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የተዘጋጀ መመሪያ ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የአንድ ከተማ የመንገድ ጥራት የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ የማሻሻያ አንዱ መሳሪያ ነው፡፡ በተጨማሪም መንገድ ለተለያዩ ተዛማጅ አገልግሎቶች ሊውል ይችላል፡፡

ይህንኑ መሰረት በማድረግ ከዚህ በፊት 80% በላይ የሚሆነውን የከተማውን የመሬት ሽፋን በአዲስ አበባ ከተማ ፕላንና ልማት ኮሚሽን ተብሎ በሚጠራ ጊዜ ጥናቱ ከተከናወነ በኋላ ጥናቱን ለመተግበር የሚረዱ በነሐሴ 2010 ዓ.ም እና በጥር 2011 ዓ.ም ሁለት የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ማንዋሎች ተዘጋጅተው በፕላን ተግባሪ ተቋማት ሲተገበር ቆይቷል፡፡

እነዚህ በተለያየ ጊዜ የተሰራውን የውስጥ አሰራር መመሪያዎችና ማንዋሎች ለአገልግሎተ አሰጣጥ በሚያመች መንገድ በማዘጋጀት በተበታተነ መልኩ የነበረውን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ማንዋል በአንድ የማሰባሰብ እና ከዚህ ቀደም በውስጡ አላሰራ ያሉ የማኑዋሉን ክፍሎችን በማሻሻል በመመሪያ ደረጃ ማሳደግ በማስፈለጉ ይህ መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

## 4. የመመሪያው ይዘት

### 4.1. የመመሪያው አወቃቀርና አደረጃጀት

በአጠቃላይ ሲታይ መመሪያው በሁለት ዋና ዋና መሠረታዊ ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡ እነዚህም፡-

ሀ. የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት አፈጻጸም

ለ. ጥያቄ አቀራረብ፣ምላሽ አሰጣጥ፣ የማጽደቅና መረጃ አደራረጀት ናቸው፡፡

ይህ መመሪያ አራት ክፍሎች እና ሀያ ሦስት አንቀፆች ያሉት ሲሆን በእነዚሁ ስርም ንዑሳን አንቀፆች ተካትተውበታል፡፡

## ክፍል አንድ

## 5. ጠቅላላ

### 5.1. አጭር ርእስ

**አንቀጽ 1**

ይህ መመሪያ "የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት መመሪያ ቁጥር 2/2016' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

የውስጥ ለውስጥ መንገድ መንገድ ጥናት በመመሪያው ትርጉም ላይ እንደተቀመጠው ወደ ባለይዞታዎች ቤት የሚያደርስ ለሞተር እና ሞተር አልባ ተሽከርካሪ እንዲሁም ለእግረኛ አገልግሎት የሚሰጥ መንገድ ሆነው ስፋታቸው ከ15 ሜትር በታች የሆነ መንገድ ነው፡፡ በመዋቅራዊ ፕላን አዋጁ ከተቀመጡት የመንገድ ተዋረድ ዓይነቶች የመንገድ መረብ መሬት

አጠቃቀም ምድብ በሚከተሉትት ሶስት ዝርዝር ምድቦች እና መለያ ኮዶች ተለያይቶ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑም ሆነ በመንገድ እና መጓጓዣ መረብ ፕላኑ በተወሰነው መሰረት፡-

ሀ) ዋና መንገድ AS፤

ለ) መለስተኛ ዋና መንገድ SAS፤ እና

ሐ) መጋቢ መንገድ CS ሲሆኑ በመዋቅራዊ ፕላን አዋጁ ላይ እንደተቀመጠው የውስጥ ለውስጥ መንገድ በከተማ ፕላን የአሰራር ደንቦች፣ ሙያዊ ልምዶችና ደረጃዎች መመሪያ እና ኮሚሽኑ በሚያዘጋጀው ዝርዝር ዲዛይን መሰረት የሚወሰን ይሆናል በሚል ተደንግ በተቀመጠው መሰረት የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናትም ይህንኑ መሰረት ተደርጎ ትርጉም ተሰጥቶ የሚከነወን ተግባር ነው፡፡

## 5.2. ትርጓሜ

**አንቀጽ** 2

በዚህ አንቀጽ ስር በመመሪያው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላትና ሐረጎች ለመመሪያው አፈጻጸም ሲባል ይዘታቸው ተተርጉሞ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

**አንቀጽ** 2(5)

"**መንገድ ተዋረድ**' ማለት መንገዶች በስፋታቸው መጠን እና በሚሰጡት አገልግሎት የተወሰነ የመንገድ ዓይነት ነው፤

**አንቀጽ** 2(6)

"**የወንዝ ዳር መጠበቂያ**' ማለት በከተማ መሃል አቋርጠው የሚያልፉትን ጅረቶች እና ትላልቅ ወንዞችን ከአካባቢው ነዋሪዎች ጣልቃ ገብነት ለመከላከል እንደ የወንዞቹ ስፋት በግራና ቀኝ የሚከለል ወሰን ነው፡፡

**አንቀጽ** 2(7)

"**የውስጥ ለውስጥ መንገድ' ማለት** ወደ ባለይዞታዎች ቤት የሚያደርስ ለሞተር እና ሞተር አልባ ተሽከርካሪ እንዲሁም ለእግረኛ አገልግሎት የሚሰጥ መንገድ ሆነው ስፋታቸው ከ15 ሜትር በታች የሆነ ነው፤

**አንቀጽ** 2(8)

"**ከረጢት መንገድ**" ማለት ቁጥራቸው አንድ እና ከአንድ በላይ ለሆኑ ይዞታዎች የሚያገለግል ዘላቂነት የሌለው መንገድ ነው፤

**አንቀጽ** 2(9)

"**የመንገድ ርቀት** ' ማለት ከአንድ የውስጥ ለውስጥ መንገድ እስከ ሌላኛው የውስጥ ለውስጥ መንገድ የሚኖረው ርቀት ነው፤

**አንቀጽ** 2(10)

"**የመንገድ ስፋት**' ማለት የተለያየ ደረጃ ያላቸው መንገዶች የጎን ስፋት ነው፡፡

**አንቀጽ** 2(11)

**መጋጠሚያ ቦታዎች**' ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ ሲሆን መታጠፊያ ላይ ቢያንስ 3 ሜትር ራዲየስ የሚያስፈልገው ቦታ ነው::

**አንቀጽ** 2(12)

"**ስልታዊ የልማት ቦታዎች**" ማለት በመዋቅራዊ ፕላን የተቀመጠውን ዕቅድ ለማስፈጸም እንዲቻል ቅድሚያ ተሰጥተው ሊፈጸሙ፣ በበጀት ሊደገፉ የሚገባቸውን የስራ ዓይነቶች በመለየት በአጭርና በመካከለኛ ዘመን በእቅድ ለይቶ ለመፈጸም እንዲቻል በመዋቅራዊ ፕላኑ ላይ ተመላክተው የተቀመጡ ቦታዎች ናቸው፤

**አንቀጽ** 2(13)

"**ማዕከላት**" ማለት በመዋቅራዊ ፕላኑ ዋና ዋና አገልግሎቶች እና ሥራዎች ተሰባስበው የሚገኙበት እና በፕላን የተመላከቱበት ቦታ ነው፡፡

በዚህ መመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉና በአዋጅ 52/2009 እንዲሁም ደንብ ቁጥር 130/2014 ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት እና ሀረጎች በዚህ መመሪያ ላይ ጥቅም ላይ ሲውሉ ተመሳሳይ ትርጉም እና ይዘት ያላቸው ሆነው በመገኘታቸው በአዋጁ እና ደንቡ ላይ የተሰጣቸውን ትርጓሜ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውጪ በዚህ መመሪያ ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን ቃላት እና ሐረጎች በዚህ አንቀጽ ከፍ ብሎ በተገለጸው አግባብ ትርጉም እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡

### 5.3. የተፈጻሚነት ወሰን

**አንቀጽ** 3

የዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ወሰን በዋነኝነት ተግባራዊ የሚሆነው ጸድቆ በስራ ላይ ባለው በአዲስ አበባ ከተማ 10ኛው መዋቅራዊ ፕላን ተፈፃሚ በሚሆንባቸው የከተማው ቦታዎች ሆኖ ከአስራ አምስት ሜትር በታች ስፋት ባላቸው መንገዶች ላይ፤ በኢንዱስትሪ መንደሮች ደግሞ ሀያ ሜትር እና በታች ስፋት ባላቸው በከተማው ክልል የሚገኙ

መንገዶችን ለማዘጋጀት፣ ለማሻሻልና ለመለወጥ ተፈጻሚ እንዲሆን የተዘጋጀ መመሪያ ነው፡፡

## ክፍል - ሁለት

### 6. የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት አፈጻጸም

**አንቀጽ** 5(1)

መመሪያው ተግባራዊ ሲደረግ የመሬት አጣቃቀም ምድባቸው በቅይጥ መኖሪያ እና ቅይጥ የንግድ ቦታዎች ሊኖራቸው የሚችለው የውስጥ ለውስጥ መንገድ መዳረሻ ስፋቱ ከ10 ሜትር እንደማይበልጥ የሚያስቀምጥ ቢሆንም በአንዳንድ ትላልቅ የህንፃ ግንባታ ባለባቸው፣ በታሪካዊ በሆኑ እና ጥበቃ በሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች መንገዱ ቀድሞ የነበረውን የመንገድ ስፋት ጠብቆ እንዲሄድ የሚደረግ ሆኖ ነገር ግን ትንሹ የመንገድ ስፋት ግን ከ6 ሜትር እንደሌለበት ያስቀምጣል፡፡

**አንቀጽ** 5(3)

የ4 ሜትር ከረጢት መንገድ ስፋት ያለው ከሆነ ግን ከአንድ ይዞታ ለማይበልጥ መግቢያ እና መውጫ መዳረሻ መንገድ ብቻ ሆኖ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 5(5)

መንገዱ ከአንድ በላይ ይዞታዎች እንዲያስተናግድ ሲፈለግ የሚዘጋጀው ከረጢት መንገድ ስፋቱ ከ6 ሜትር በታች ሊሆን አይችልም፡፡

ከረጢት መንገድ በአብዛኛው ወደ ይዞታ እንዲያደርስ ተደርጎ የሚዘጋጅ መንገድ ቢሆንም በዋነኝነት የመንገድ ስፋቱ በሚያስተናግደው የተሽከርካሪ ብዛት የሚወሰን እንደሆነና ይህም በዚህ አንቀጽ ላይ በግልጽ የተቀመጠበት እና ይህንኑ መሰረት ተደርጎ መፈጸም እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

**አንቀጽ** 5(6)

በመመሪያው በዚህ አንቀጽ ከታዩት ጉዳዮች ውስጥ ሽንሻኖ በሌላቸው ሰፋፊ ቦታዎች በፕላኑ ግን ለቅይጥ አገልግሎት የታቀዱ ቦታዎች ላይ የሚቀርብ የተናጠል የመዳረሻ

መንገድ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችለው በቅድሚያ ለጠቅላላ ቦታው የሽንሻኖ ሥራ በመሬት ልማት እና አስተዳደር አማካኝነት ሲካሄድ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦ ሆኖም ግን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት የሚጠየቅለት አካባቢ ጠቅላላ የቦታዉ ስፋት ከ5 ሄክታር ሊበልጥ አይችልም፤

**አንቀጽ** 5(8)

የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት የተጠየቀለት አካባቢ የቦታ ስፋቱ ከ5ሄክታር በላይ ከሆነ ግን ለቦታዉ የአካባቢ ልማት ፕላን ሊኖረዉ የሚገባ ሲሆን ፕላኑም በቢሮው ተዘጋጅቶ ይጸድቃል፤

በማህበራት ወይም በሽንሻኖ ተላልፈው በመዛነፍ ምክንያት በውስጥ ለውስጥ የመንገድ ጥናት ያልተካተቱ ከ5 ሄክታር በላይ ይዞታዎች ሲያጋጥም በወቅቱ ለአገልግሎትና አረንጓዴ የተያዙ ቦታዎች ባሉበት እንዲጠበቁ ተደርጎ መንገዱ ተሻሽሎ እንዲጠና ማድረግ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ** 6

ለአምልኮ ማካሄጃ አዲስ ለሚመደብ ቦታዎች የመዳረሻ መንገዱ ስፋት ቢያንስ 15 ሜትር ስፋት ያለው ሰብሳቢ መንገድ መሆን አለበት፤ ሆኖም ግን ነባር የአምልኮ ይዞታዎች ሆነው የመንገድ ስፋቱ 15 ሜትር ማስመር (ማጥናት) የማይቻል ከሆነ ግን ቢያንስ 6 ሜትር መንገድ በማስመር አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡

**አንቀጽ** 7(1)

በመመሪያው በቅይጥ መኖሪያ መሬት አጠቃቀም ምድብ ውስጥ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት በሚሰጡ አዲስ ቦታዎች ላይ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ስፋት ከ15 እስከ 20 ሜትር መሆን ያለበት ሲሆን ለአንድ የኢንዱስትሪ ተቋም መግቢያ ብቻ ከሆነ የ10 ሜትር ከረጢት መንገድ ሊሆን እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡

**አንቀጽ** 7(2)

ሆኖም ግን የመሬት አጠቃቀሙ ሙሉ በሙሉ ለኢንዱስትሪ ዞኖች ዉስጥ ለሚገኙ ቦታዎች የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ስፋት ከ20 ሜትር በታች መሆን እንደሌለበት ያስቀምጣል፡፡

**አንቀጽ**7(3)

ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ቀደም ሲል ከ10 ሜትር እስከ 15 ሜትር ተሰምሮ ካርታ የወሰዱ በኢንዱስትሪ ዞኖች የሚገኙ ባለይዞታዎች መንገዱን ወደ

20 ሜትር ለማሻሻል የሚያስችል ትርፍ መሬት ከሌለ ወይም ከእነርሱ ይዞታ ተቀንሶ እንዲሰራ ፍቃደኛ ካልሆኑ በነበሩበት እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 8(1)

በዚህ መመሪያ ከሚታዩ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ በወንዝ አካባቢ ስለሚጠኑ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሲሆን በጥናቱ ወንዝ ማቋረጥ የሚቻለው በየ500 ሜትር ርቀት ባለ ሰብሳቢ መንገዶች ሆኖ ከዚህ ቀደም በነበሩ እና በቆዩ አካባቢዎች በየ500 ሜትር ርቀት ሰብሳቢ መንገድ በማይኖሩበት ሁኔታ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ወንዝ እንዲያቋርጡ ማድረግ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ** 8 (2)

በወንዝ ዳርቻ ያሉ አረንጓዴ መናፈሻዎች የአካባቢ ልማት ፕላን ፀድቆ በሚለማበት ወቅት የውስጥ ለውስጥ መሻገሪያ ድልድይ ከ 4ሜትር ስፋት ጀምሮ ሊገነባ ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 8(3)

በወንዝ ዳር መጠበቂያ 4ሜትር የእግረኛ መንገድ ሊኖር ይችላል፤ ሆኖም የወንዝ ዳር መጠበቂያ መንገድ የይዞታዎች መዳረሻ ከሆነ ቢያንስ 6ሜትር የመንገድ ስፋት ሆኖ እንደሚኖሩት ይዞታዎች ብዛት በፕላን ሊያዝ ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 8(4)

በወንዝ ዳርቻዎች መንገድ በሚጠናበት ጊዜ ከወንዝ መጠበቂያው ጀምሮ ወደ ውጭ ግንጥል ርቀት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ አንቀጽ ላይ እንደሚያመለክተው በወንዝ ዳርቻ አካባቢ መንገድ በሚጠና ጊዜ የመንገድ ጥናቱ ሊጠና የሚገባው በስታንዳርዱ እንደተቀመጠው መንገዱ የወንዝ ዳርቻውን ለማስጠበቅ በተቀመጠው መሰረት ተደር የወንዝ መጠበቂያውን ሳያካትት መሆን እንዳለበት የሚያስቀምጥ ሲሆን ይህ የሆነበት ምክንያት ለወንዝ መጠበቂያ ተብሎ የሚተወው ቦታ ዓላማውን ስቶ ለመንገድ አገልግሎት እንዳይውል እና አካባቢውን ለመጠበቅ እንዲሆን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ** 9(1)

የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በፀደቀ የአካባቢ ልማት ፕላን ካልሆነ በስተቀር ጥብቅ የአረንጓዴ ቦታዎችን ሊያቋርጡ አይገባም፡፡

**አንቀጽ** 9(2)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጥብቅ የአረንጓዴ ቦታዎቹ በሌላ አገልግሎት እንዳይጣሱ እና ለእግረኛ እንቅስቃሴ

እንዲያመቹ ጥብቅ የአረንጓዴ ቦታዎችን እንዲከብቡ ማድረግ ይቻላል፡፡

**አንቀጽ** 10(1)

የከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ የኤሌክትሪክ መስመር መጠበቂያ ክልል ውስጥ የውስጥ ለውስጥ መንገድ አይሰመርም ወይም አይጠናም፡፡ ይህም የኤሌክሪክ መስመሩ ተሸክሞ ከሚሄደው የኤሌክትሪክ ኃይል አንጻር መንገዱን በሚገለገለው አካል ላይ ሊደርስ ከሚችለው አደጋ ለመከላከል ታሳቢ የተደረገና ለዚህ ተብሎ የተተወው ቦታ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ** 10(2)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ዳርቻ ላይ ያሉ ነባር ይዞታዎች ባሉበት መዳረሻ መንገድ ለመስጠት ሲባል የ6 ሜትር መንገድ ዳርቻውን ይዞ ሊሰመር ይችላል፤

**አንቀጽ** 10(3)

በከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ ኤሌክትሪክ ባለበት አካባቢ መንገድ በሚጠናበት ጊዜ ለኤሌክትሪክ መስመሩ መጠበቂያ በተያዘው ቦታ ላይ ሳይሆን ከመጠበቂያው ጀምሮ ወደ ውጭ በማድረግ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 11(1)

የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ሲጠኑ ምጣኔ ሃብታዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ የሆኑ ቦታዎችን መንካት የለባቸውም፡፡

**አንቀጽ** 11(2)

ከዚህ በፊት በ6ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በፕላን የተሰሩ አካባቢዎች የሚኖረውን ምጣኔ ሃብታዊ ተጽእኖ ከግንዛቤ በመውሰድ የአንድ አቅጣጫ የመኪና መንገድ በማድረግ በ6ሜትር እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 11(3)

ትልቅ ግንባታ ያረፈባቸው ቦታዎችም የሚኖራቸውን የመንገድ ስፋት ይዘው እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 11(4)

ከዋና እና መለስተኛ መንገድ ጋር የተገናኙ እና ለአካባቢው ነዋሪ የመግቢያና መውጫ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ከዋና መንገድ ጋር በሞተር

ተሽከርካሪ እንዳይገናኙ መደረግ አለበት፤ከዋና መንገድ ጋር መገናኘት የሚችሉት በሌላ አቅጣጫ ባለ ሰብሳቢ መንገድ አማካኝነት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 11(5)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት የተጠቀሰው አማራጭ በሌለበት ጊዜ መንገዱ ለቀኝ ታጣፊ ተሽከርካሪ ብቻ እንዲያገለግል ሆኖ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ** 11(6)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዋና መንገድ ጋር የተገናኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለሞተር ተሽከርካሪ ዝግ ይሁኑ እንጂ እግረኛና የአካል ጉዳተኞች ተሽከርካሪን እንዲያሳልፉ ተደርገው ይሰራሉ፡፡

**አንቀጽ** 11(7)

ከዚህ ቀደም የ10 ሜትር ስፋት በላይ ያላቸው ነባር የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ባላቸው ስፋት እንዲጠበቁ ተደርገው ይያዛሉ፡፡

**አንቀጽ** 11(8)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 ያለው ኃሳብ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንገድ ስፋቱ በነበረው የማይቀጥል ሆኖ ከተገኘ ከሚሰመረው የመንገድ ስፋት በላይ ያለው የሚተርፈው ቦታ በቀጣይ ጥናት ለአካባቢው ማስዋቢያ ለአረንጓዴ ሽፋን እንዲውል ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 12(1)

በ10 ዓመት መልሶ ማልማት ፕላን በሚሰራላቸው እና የኮሪደር ልማት ፕላን በሚጠናላቸው ቦታዎች የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የተጠናላቸው ሲሆን በአካባቢው ላይ የሚመጡ የልማት ጥያቄዎች በውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጥናት መመሪያ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 12(2)

በ5 ዓመት የመልሶ ማልማት እና የኮሪደር ልማት በሚሰራላቸው ቦታዎች ላይ የአካባቢ ልማት ፕላን ጥናት ውስጥ በዝርዝር መንገዶቹ እንዲጠኑ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 12(3)

የአካባቢ ልማት ፕላን እስኪዘጋጅላቸው በነባር ይዞታዎች ላይ የማልማት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አካላት የ8 ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገዱ ይዘጋጃል፡፡

**አንቀጽ** 12(4)

የ2ኛ ደረጃ፣ 3ኛ ደረጃ እና ልዩ ማዕከላት ተብለው በተያዙት ቦታዎች የማልማት ጥያቄ

የሚስተናገደው በተጠየቀበት ቦታ ከሰብሳቢ መንገድ ጋር ተመጋጋቢ የሆነ ከ8 ሜትር የማያንስ ዘላቂ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በፕላን በማመላከት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 12(5)

የ4ኛ ደረጃ ወይም የወረዳ ማዕከላት ተብለው በተያዙት ቦታዎች ላይ የአካባቢ ልማት ፕላን ሲጠና ተግባራዊ ይሆናል፤ ሆኖም ግን ቦታው በፕላን ለተቀመጠለት ዓላማ የማልማት ጥያቄ ሲቀርብ 8 ሜትር ዘላቂ መንገድ በፕላን በማመላከት የሚለማ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 12(6)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተደነገገው ቢኖርም በቦታው ላይ የግለሰብ ባለይዞታዎች ካሉ እና የይዞታ ነክ አገልግሎቶችን የሚጠይቁ ከሆነ የመንገድ ጥናት ከሚጠይቁ አገልግሎቶች ውጪ ያሉ አገልግሎቶችን መስጠት ይቻላል፡፡

**አንቀጽ** 12(7)

በስልታዊ ቦታዎች ላይ የአካባቢ ልማት ፕላኖች ሲጠኑ በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱትን የውስጥ ለውስጥ መንገዶች መጠበቅ ካልተቻለ መንገዶቹን ከመሬት አጠቃቀም ጋር ተጣጥሞ እንዲጠና ማድረግ ይቻላል፡፡

# ክፍል ሦስት

## 7. የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት

### ጥያቄ አቀራረብ ፣ ምላሽ አሰጣጥ፣ የማጽደቅ እና መረጃ አደረጃጀት

**አንቀጽ** 13(1)

የውስጥ ለውስጥ መንገድ መስተንግዶን በሚመለከተ ቢሮው ወይንም ጽ/ቤቱ ጥያቄዎችን ከሚቀበልበት አሰራር አንዱ የይጠናልኝ ጥያቄ መስተንግዶ ሊያገኝ የሚችለው ጉዳዩ ከሚመለከተው ፕላን ተግባሪ ተቋም በደብዳቤ ጥያቄ ሲቀርብ አንዱ መንገድ ነው፡፡

**አንቀጽ** 13(2)

ሌላው ከመንገድ ጥናት ጋር በተያያዘ ጥያቄ ወይም አቤቱታ ያላቸው ተገልጋዮች ጥያቄአቸውን ለቢሮው ወይም ለጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ** 13(3)

ማንኛውም የመዳረሻ መንገድ ጥያቄ በቢሮ ወይም በጽህፈት ቤቱ ሊስተናገድ የሚችለው ጥያቄው ጉዳዩ በሚመለከታቸው የፕላን ተግባሪ ተቋማት ኃላፊዎች ፊርማ በጽሁፍ ሲላክ ብቻ ነው፡፡ የመንገድ ይጠናልኝ ጥያቄ በዋነኝነት ሊቀርብ የሚገባው ፕላኑን ከሚተገብሩ

ተቋማት ሲሆን ጥያቄው ሊቀርብ የሚገባው የተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች አውቀውት በጽሁፍ በተደራጀ መልኩ ሊሆን ይገባዋል፡፡

**አንቀጽ** 13(4)

የውስጥ ለውስጥ መንገድ እንዲዘጋጅለት ጥያቄ የሚያቀርብ ፕላን ተግባሪ ተቋማት የሚከተሉትን መረጃ አሟልተው እንዲያቀርቡ ይጠበቃል፡-

ሀ) መንገድ የሚጠናለትን ይዞታ x እና y ኮኦርድኔት፤

ለ) የይዞታውን የሚገልጽ የተቋሙን በቤዝ ማፕ የተደራጀ መረጃ፤

ሐ) ካርታ ካለው ካርታ ኮፒ ( የካርታውን ሶፍት ኮፒ በሲዲ)፤

መ) በጂ.አይ.ኤስ የሚታይ ከሆነ የጂ.አይ.ኤስ መረጃ፤

ሠ) ከይዞታ ይካፈልልኝ ጋር የተያያዘ ከሆነ የሚከፈሉትን ይዞታዎች እና አጎራባች ቦታዎች ፕላን ፎርማት በማመላከት፤

ረ) የሚጠናውን ቦታ በፕላን ፎርማት በወቅታዊ ቤዝማፕ በማመላከት መረጃዎችን በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ መላክ ወይም ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ** 13(5)

ከመንገድ ጥናት ጋር በተያያዘ ቅሬታ ወይም አቤቱታ ለቢሮው ወይም ለጽህፈት ቤቱ የሚያቀርቡ ተገልጋዮች ይዞታውን የሚመለከት ህጋዊ ሰነድ እንዲሁም የሚያቀርቡትን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡ ከመንገድ ጥናትም ሆነ ከጥናቱ ጋር በተያያዘ በዋነኝነት ተገልጋይ ግለሰቦች ቅሬታ ወይንም አቤቱታ ሲኖራቸው ጥያቄአቸው ተቀባይነት የሚያገኘው በመጀመሪያ ደረጃ ለይዞታው ህጋዊ የሰነድ ማስረጃ ሲኖራቸው እንዲሁም ቅሬታቸውን ወይም አቤቱታቸውን ግልጽ በሆነ መንገድ በጽሁፍ ለቢሮው ወይንም ለጽቤቱ ሲያቀርቡ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

**አንቀጽ** 14(1)

ለቢሮው ወይም ለጽህፈት ቤቱ ፕላን ተግባሪ ተቋማት የውስጥ ለውስጥ መንገድ እንዲዘጋጅላቸው ጥያቄ ባቀረቡ በ15 ቀናት ውስጥ እንደ ቅደም ተከተላቸው ምላሽ መሰጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ** 14(2)

ምላሽ ሲሰጥ መዋቅራዊ ፕላኑ በተደራጀበት መስመር ካርታ መሰረት ተደርጎ አስፈላጊውን የመንገድ ጥናት በሀርድ እና በሶፍት ኮፒ በፕላን ፎርማት አስደግፎ የሚላክ ሲሆን

ፀድቀው የተላኩ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የሚል አርእስት ባለው ሰንጠረዥ በማዘጋጀት የወሩ ስም እና ቀን የስም ዝርዝሩን ፣ወረዳ፣ኮኦርድኔት በማካተት ሊላክ ይገባል፡፡

**አንቀጽ** 14(3)

ጽህፈት ቤቶች ባዘጋጁት የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ላይ ሙያዊ አስተያየት ያስፈልገናል ብለው ካመኑ ለቢሮው የፕላን ዝግጅት ዘርፍ በደብዳቤ ወይም በአካል በመቅረብ መጠየቅ ይችላሉ፣ ዘርፉም በ5 የስራ ቀናት ውስጥ አስተያየት ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ** 14(4)

ከውስጥ ለውስጥ መንገድ ጋር በተያያዘ ከተገልጋዮች በግል ለቀረቡ ጥያቄዎች ቢሮው ወይም ጽህፈት ቤቱ በዚህ መመሪያ የተቀመጠው የመንገድ ጥናት አሰራር መሰረት አድርጎ ምላሽ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ** 14(5)

በቢሮው የሚገኘው የፕላን አፈፃፀም ክትትል ዘርፍ ቢያንስ በ3 ወር አንድ ጊዜ በቢሮውም ሆነ በክፍለ ከተሞች በሚዘጋጁ የመንገድ ጥናት መረጃዎች ላይ የጥራት ኦዲት ክትትል በማድረግ የአፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡

**አንቀጽ** 15(1)

በማህበር ተደራጅተው ወይም በሌላ በተመሳሳይ መንገድ ወጥ በሆነ ሽንሻኖ ቦታ የተሰጣቸው ህጋዊ ባለይዞታዎችን ቦታ በመቀነስ ለመንገድ ማስፋፊያ ማዋል አይቻልም፣ ይሁንና የመንገዱ መሻሻል በራሳቸው ከጠየቁና ሁሉም ባለይዞታዎች ከተስማሙ መንገዱን ማሻሻል ይቻላል፡፡

**አንቀጽ** 15(2)

የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ሲጠኑ አጥር ወይም ግንባታ የሚነካ ከሆነ የነዋሪዎች ስምምነት መኖሩ በጥናት ተረጋግጦ መንገድ መጠናት አለበት፣ ሆኖም ነባራዊ መንገዱ ከ4 ሜትር በታች ከሆነ እና ይዞታው አማራጭ መዳረሻ መንገድ የሌለው ከሆነ እና የግንባታው መውጫ የተዘጋ መሆኑ ከተረጋገጠ አነስተኛ ተጽእኖ እንዲኖረው ተደርጎ በግራና በቀኝ እኩል በማድረግ መከፈት አለበት፡፡

**አንቀጽ** 15(3)

በቢሮው ወይም በጽ/ቤቱ ተጠንተው በሥራ ላይ የዋሉ መንገዶች ችግር አጋጥሞ እንዲለወጡ ከተቋማት በደብዳቤ ጥያቄ እስካልቀረበ ድረስ ባሉበት እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 15(4)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚመለከተው ተቋም የህብረበተሰቡን ጥያቄ መነሻ በማድረግና በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ችግር ይፈጥራል ተብሎ ሲታመንበት በደብዳቤ አማራጮችን በመጠቆም ለቢሮው በማቅረብ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ** 15(5)

ጽህፈት ቤቱም ከዚህ ቀደም ተጠንተው በሥራ ላይ የዋሉ መንገዶች መሻሻላቸው አግባብነት ያላቸው መሆኑን ሲያምን በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ሀሳቦችን በመጠቀም ለቢሮው አቅርቦ ሲፈቀድ ማሻሻያ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 15(6)

ቢሮውም ሆነ ጽህፈት ቤቱ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የሚያዘጋጁት በዋናነት የመዋቅራዊ ፕላኑ በተደራጀበት መስመር ካርታን በመጠቀምና አስፈላጊ ከሆነ በመስክ ላይ ተገኝቶ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 15(7)

ማንኛውም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ በሚሰጥበት ጊዜ ይዞታውን የሚያዋስን የውስጥ ለውስጥ መንገድ መኖሩ መረጋገጥ ይኖርበታል፤ ሆኖም ግን በይዞታ እና በመንገድ መካከል ከ7 ሜትር በላይ ክፍተት ሲኖር በባለይዞታውና በመንገዱ መካከል ሌላ ይዞታ አለ ተብሎ ስለሚታሰብ ባለይዞታው ግንባታ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡

**አንቀጽ** 15(8)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) የተደነገገው ቢኖርም በመስክ ተወርዶ በቦታው ላይ ግንባታ አለመኖሩን በማረጋገጥ እና የቤዝ ማፕ መረጃ ተረጋግጦ መንገድ እንዲጠናለት ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 15(9)

አንድ ይዞታ ለሁለት ወይንም ከዛ በላይ ለሆነ ቦታዎች የማካፈል ጥያቄ ሲቀርብ የሚካፈሉት ቦታዎች የመዳረሻ መንገድ ሊያገኙ ይገባል፤ ሆኖም ግን ሲካፈሉ አንዱ ቦታ መንገድ ማግኘት ካልቻለ የመዳረሻ መንገድ ሊወጣለት የሚችለዉ እንዲካፈል ከሚፈልገዉ ቦታ ተወስዶ እና ይዞታው ሲካፈል ለቦታው የተመደበውን አነስተኛ የህንፃ ከፍታ ሊያሰራ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ** 15(10)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (10) ከተመለከቱት ውጪ የሚካፈሉት ቦታዎች የመዳረሻ መንገደ ማግኘት ካልቻሉ ቦታዉን ማካፈል አይቻልም፡፡

**አንቀጽ** 15(11)

ፕላን ፈጻሚ ተቋማት እንዲጠናላቸው የሚፈልጉአቸው ቦታዎች በካርታ መዛነፍ እና ሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች የአጎራባች ቦታዎች የቅየሳ ስራ የሚያስፈልገው ከሆነ መረጃውን ከመስክ ላይ ሰብስበው የመላክ ግዴታ አለባቸው፡፡

**አንቀጽ** 15(12)

በቀደመ ፕላን መዳረሻ መንገድ ተጠንቶላቸው እና በዚያም መሠረት የተስተናገዱ ባለይዞታዎች ሲኖሩ እና ተጠንቶ የነበረው መንገድ በተላከው የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ላይ የተነሳባቸው ሆኖ ሲገኝ ለባለ ይዞታው መዳረሻ ሊሰጥበት የሚችልበት የተሻለው አማራጭ ተመዝኖ መዳረሻ ይሰጠዋል፡፡

**አንቀጽ** 15(13)

መግቢያቸው መዋቅራዊ ፕላኑ በተደራጀበት መስመር ካርታ ላይ የማይታይ፤ መዳረሻቸው ያልታወቁ ይዞታዎች በሚያጋጥምበት ጊዜ በመስክ ምልከታ በተደገፈ መረጃ የመዳረሻ መንገድ መከፈት ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ** 15(14)

በመልሶ ማስፈሪያ አካባቢ ዝርዝር ጥናት ካልተዘጋጀ በተናጠል ለአንድ ይዞታ መዳረሻ መንገድ ማዘጋጀት አይቻልም፡፡

**አንቀጽ** 15(15)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (15) የተደነገገው ቢኖርም ቀደም ሲል ህጋዊነት ባለው አግባብ ቦታ ይዘው በመልሶ ማስፈሪያ ቦታዎች የሚገኙ ባለይዞታዎች ከግንባታ ፈቃድ ጋር ከተያያዙ አገልግሎት በስተቀር ከይዞታ ጋር የሚገናኙ መንገድ ጥናት የማይጠይቁ አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ** 16(1)

በቢሮው የፕላን ዝግጅት ዘርፍ ኃላፊው፣ በክፍለ ከተማ ደረጃ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ከመሬት ተቋማት የሚቀርቡ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ጥያቄዎችን አግባብነት አይቶ ሲወስን ለቢሮው ስፓሻል ፕላን ዝግጅት ዳይሬክተር ለክፍለ ከተማው ስፓሻል ፕላን

ዝግጅት ቡድን እንዲሰራላቸው በፅሁፍ ያሳውቃል/ይመራል፡፡

**አንቀጽ** 16(2)

የቢሮው ስፓሻል ፕላን ዝግጅት ዳይሬክተር ወይም የክፍለ ከተማው ስፓሻል ዝግጅት ቡድኑም የቀረበው ጥያቄ የተሟላ መረጃ መያዙን በመመርመር ያልተሟላ መረጃ ከሆነ የጎደለውን መረጃ በማስታወሻ ለዘርፍ ኃላፊ/ለጽህፈት ቤት ኃላፊ በአንድ ቀን ውስጥ ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ** 16(3)

የቢሮው ዘርፍ ኃላፊ ወይም የክፍለ ከተማው የጽህፈት ቤት ኃላፊም የጎደለውን መረጃ በአስቸኳይ እንዲላክ በእለቱ በደብዳቤ ለሚመለከተው የመሬት ተቋም ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ** 16(4)

በቢሮ ስፓሻል ፕላን ዝግጅት ዳይሬክተር በክ/ከተማ ደግሞ የስፓሻል ፕላን ዝግጅት ቡድን የተሟላ መረጃ የቀረበባቸውን ጥያቄዎች በማየት አዲስ የመዳረሻ መንገድ መዋቅራዊ ፕላኑ በተደራጀበት መስመር ካርታ በማስመርና በቦታው ላይ ተገኝቶ በማረጋገጥ የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮው ዘርፍ ኃላፊወይም ለክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ያቀርባል፡፡

**አንቀጽ** 16(5)

የቢሮው ዘርፍ ኃላፊወይም የክፍለ ከተማ የጽህፈት ቤት ኃላፊም የቀረበው ጥናት በዚህ መመሪያ በተቀመጡ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች ላይ ተመስርቶ የተሰራ መሆኑን በማረጋገጥ ያፀድቃል፡፡

**አንቀጽ** 16(6)

አጠቃላይ የመንገድ ጥናቱን ቃለ ጉባኤ፣ ከተቋማት ጥያቄ የቀረበበት ደብዳቤና አባሪ የተደረጉ መረጃዎች ለተቋማቱ ጸድቆ የተላከበት ደብዳቤ እንዳስፈላጊነቱ በሶፍትና በሀርድ ኮፒ ፋይል ተዘጋጅቶላቸው እንዲቀመጡ እና ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እንዲላክ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ** 16(7)

በመረጃ ጉድለት ምክንያት ወደ መሬት ተቋማት የሚመለሱ የጥናት ጥያቄዎች መረጃቸው ተሟልቶ በመጣበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ታሳቢ በማድረግ ምላሽ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 17(1)

ከውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ጋር በተያያዘ ቅሬታ የሚያቀርቡ ተገልጋዬች ካሉ ቅሬታቸውን ጉዳያቸውን ለያዘው በቢሮው ከሆነ ለዘርፍ ኃላፊ በክፍለ ከተማ ከሆነ ጽህፈት ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ** 17(2)

ቅሬታው የቀረበለት አካል ቅሬታው በቀረበለት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ምለሽ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

**አንቀጽ** 17(3)

በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ተገልጋይ ቅሬታውን ውሳኔው በተሰጠው በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ በደረጃ አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለቢሮው ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 17(4)

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ ቅሬታው በቀረበለት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ምላሹን በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው መስጠት አለበት፤በቢሮ ኃላፊ የተሰጠ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ** 17(5)

ቅሬታ አቅራቢው በቢሮው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ አቤቱታውን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 18(1)

ውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት ጥያቄ የሚቀርብባቸው መረጃዎች ለብቻቸው ፋይል ተከፍቶ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ መረጃው ይያዛል፡፡

**አንቀጽ** 18(2)

የቢሮው ወይም የጽህፈት ቤቱ የከተማ ፕላን መረጃና ስታቲስቲክስ ዳይሬክቶሬት/ ቡድን ተጠንተው በስራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የተዘጋጀላቸውን አካላት ዝርዝር በሰንጠርዥ በማዘጋጀት ወጥ በሆነ ቤዝ ማፕ በማደራጀት በመረጃ ቋት ይይዛሉ፡፡

**አንቀጽ** 18(3)

የከተማ ፕላን መረጃና ስታቲስቲክስ ቡድን ጥናታቸው ተጠናቆ በቤዝ ማፕ ተደራጅተው በመረጃ ቋት የገቡ የውስጥ ለውስጥ መንገድ ጥናት መረጃዎች በወር ሁለት ጊዜ ለማእከል

ፕላን ዝግጅት ዘርፍ በደብዳቤ ይልካሉ፡፡

**አንቀጽ** 18(4)

የማእከል ፕላን ዝግጅት ዘርፍ መረጃዎቹን በራሱ ቋት አደራጅቶ ኮፒውን በቢሮው የመረጃ ቋት እንዲደራጅ ለከተማ ጥናት መረጃና አቅም ግንባታ ዘርፍ ይልካል፡፡

**አንቀጽ** 18(5)

የከተማ ጥናት፣ መረጃ እና አቅም ግንባታ ዘርፍ በክፍለ ከተሞች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ የመዳረሻ መንገዶች መረጃ ከፕላን ዝግጅት ዘርፍ ሲላክለት በከተማው የመረጃ ቋት በቤዝ ማፕ ተደራጅተው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ** 18(6)

የከተማ ጥናት፣ መረጃ እና አቅም ግንባታ ዘርፍ መረጃውን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ አደራጅቶና ወቅታዊ አድርጎ ለሚመለከታቸው የፕላን ተግባሪ ተቋማት በየሩብ አመቱ ያሰራጫል፡፡

**አንቀጽ** 18(7)

ቀደም ሲል በመረጃ ቋት ገብተው የተደራጁ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች የጥናት መረጃ በግለሰብ ወይም በተቋማት ጥያቄ ሲቀርብ በፕላን መረጃና ስታትስቲክስ ዳይሬክቶሬት አማካይነት ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡